የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

6ኛው የኢፌዲሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ3ኛ አመት የስራ ዘመኑ መጋቢት 3 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 16ኛ መደበኛ ስብሰባ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 9/2016ን ለዝርዝር እይታ በዋናነት ለውጭ ግንኙነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተባባሪነት ደግሞ ለህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቷል።

## የዚህ ረቅቅ አዋጅ መደንገግና አዲስ አዋጅ የማውጣት አስፈላጊነት

በሀገራችን እና አህጉራችን በፖለቲካ በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ሌች ዘርፎች የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ እና ሀገራዊ ዕውቅና ሽልማት ሊሰጣቸው የሚገቡ ግለሰቦች እና ድርጀቶች ያሉ ቢሆንም ይህን ማስፈጸም የሚያስችል ህግ ባለመውጣቱ ምክንያት ለግለሰቦቹ እና ድርጅቶቹ ተገቢው እውቅና ሳይሰጥ ቆይቷል።

ስለሆነም ሃገራችን ባለውለታዎቿን ክብር በመስጠት ቀጣይ ትውል በተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ተግቶ በመስራት ለክብር ለመብቃት የሚነሳሳበትን ሁኔታ በህጋዊ ስርዓት መዘርጋት ስለሚያስፈልግ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል።

## የረቂቅ አወጁ ዓላማ

1. በሀገሪቱ ብሎም በአፍሪካ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያየ ዘርፎች ለሃገር እና ህዝብ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሰው ልጆች የሚጠቅም የላቀ ተግባር የፈጸሙ ሰዎችን ወይም አካላትን እውቅና በመስጠት ሌሎች የእነሱን አርአያነት እንዲከተሉ ማድረግ፣

2. በህገ-መንግስቱ መሰረት ማስፈጸሚያ አዋጅ ሳይመጣላቸው እየተሰጡ ያሉ የተለያዩ ሽልማቶችን ወጥ የሆነ ህጋዊ አሰራር ስርዓት እንዲኖረው ማስቻል ነው።